# ግፍ በማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ!

## (በፈጠራ ወንጀል ተከሰው በማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ እየተሰቃዩ "የወገን ያለህ! የህግ ያለህ!" እያሉ ከሚገኙ የህሊና እስረኞች መካከል የተገኘ ሪፖርት!)

የምሰጠው ምስክርነት በአይኔ የአየሁትንና በውስጡም የአሳለፍኩበትን ነው። እኔ እራሴ ለአንድ ወር ተኩል በዚሁ መምሪያ ማጎሪያ እስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ግፍ ተፈፅሞብኛል፤ ይህንንም ምስክርነት የምሰጠው ህሊናዬ አስገድዶኝና የአባቶቼንና ለኢትዮጵያ ሀገራችን በከፍተኛ ትምህርታቸውና ልምዳቸው ብዙ የሰሩና እየሰሩ የአሉ ምሁራን ስቃይ እረፍት ስለነሳኝ ነው። አላማዬም የኢትዮጵያና የአለም ሕብረተሰብ እንዲሁም አገር በቀልና አለም አቀፋዊ የዜና አውታሮች የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና የእስረኞች ጉዳይ ተከታታዮች እንዲያውቁትና የበኩላቸውን ተፅእኖ እንዲያደርጉ ለመግፀን ነው።

ዋና ዋና ነጥቦችም እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ!!

- እነዚህ አዛውንቶችና ወጣቶች በቁጥጥር ስር የዋሉት "የካቲት 12 ቀን 1998 ዓ.ም. ኦፕሬሽን" በሚባለው ከለሊቱ 9 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት የካቲት 12 ቀን ንጋት ድረስ ነው።

- ሰዎቹ የተያዙት ያላንዳች የፍርድቤት ትእዛዝ የእያንዳንዳቸው መኖሪያ ቤት ሰብሮ በመግባት ነው።

- ብርበራዎች የተካሄዱት እስረኞቹ ከታሰሩና ቤተሰቦቻቸውም በአንድ ክፍል ውስጥ በታጣቂዎች ከ 3-4 ሰዓት በታጣቂዎች ታግተው ከቆዩ በኋላ ነበር።

- በአብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ቤት ውስጥ በልጆች ቁምሳጥን በአልጋ ስርና በመሳሰሉት ተዓማኒነት በሌላቸው ቦታዎች አሳሪ ፖሊሶች ራሳቸው ይዘው የመጡትን 1) ቦንቦች 2) ፈንጂዎች 3) ሽጉጦችና ልዩ ልዩ የመወንጀልያ ሰነዶች አስቀምጠዋል። በመቀጠልም የራሳቸውንና የመንግስት ተካፋይ ግለሰቦችን ታዛቢ በመያዝ እነዚህ ንብረቶች ከነዚህም አዛውንቶችና ወጣቶች ምሁራን ቤት እንደተገኙ በማስመሰል የፈጠራ ወንጀል ማስረጃ ለማድረግ እየተሞከረ ነው።

- ፖሊስ ራሱ ከሳሽ ራሱ ምስክር በመሆን ያላንዳች ሀፍረት ፍ/ቤት እነዚህን ተጠርጣሪ የሚላቸውን አዛውንቶችና ወጣቶች ፍ/ቤት አቅርቦ በቀጠሮ በማመላለስ ብቻ ክስ ሳይመሰረትባቸው ወደ ሁለት ወር አስሯቸው ይገኛሉ።

- ህገወጥ ቁሳቁስ እናገኛለን ብለው በተስፋ የሄዱበት ተጠርጣሪ (ታሳሪ) ቤት መሳሪያ ሲያጡ እንደገና በመመለስ የሚፈልጉትን መወንጀልያ በማስቀመጥ ለሁለተኛ ጊዜ ብርበራ አድርገው ህገወጥ ቁሳቁሶች እንደተገኙ በማስመሰል የፈጠራ መወንጀያ አድርገዋል።

- እነዚህ እሥረኞች በእድሜያቸው በአብዛኞቹ ከ50 — 70 አመት ሲሆን ወጣቶች ያሉበት ሙያቸውና ስራቸው ከቅንጅቱ መሪዎች ጠበቃ ጀምሮ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች የልማት አማካሪና የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች እንዲሁም ጡረተኞችም ይገኙበታል።

- በእነዚህ እስረኞች ላይ የተለመደው የመንግስት የፈጠራ ወንጀል መንግስትን በኃይል ለመገልበጥ (አሁን ደግሞ ሕገመንግስቱን በኃይል ለመናድ ይባላል!!)፣ ባለስልጣኖችንና ታዋቂ ግለሰቦችን ለመግደልና የመንግስት ተቋማትን ለማውደም ሲደልቁ እንዲሁም ለቅንጅት ተለዋጭ አመራር በመሆን አገልግሎት ሲሰጡ ይዘናቸዋል በማለት የፈጠራ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ ይገኛል፤ ይህ ማለት ሰዎቹ ከታሰሩ ወደ 2 ወር ተጠግቶአቸዋል። እስካሁን ክስ አልተመሰረተባቸውም።

- በቅንጅት ተለዋጭ አመራርነት ተጠርጥረው ከታሰሩት ውስጥ የቅንጅት አባል ያልሆኑ ሁሉ አሉበት።

- ሌሎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ፖሊስ "የቅንጅት ቅሪቶችና አሸባሪዎች" በማለት ለጤንነት በማይስማማ የምግብና የውኃ አቅርቦት በሌለበት የማጎሪያ እስር ቤቶች ታጉረዋል።

- በጣም ጠባብ 3x3 ሜትር በሚያንስ ክፍል ውስጥ ከ18 በላይ ታጉረው ሰንብተዋል፣ ለ8 ቀናት በር ተዘግቶባቸው ለመፀዳዳት ጥዋትና ማታ ለ20 ደቂቃ ብቻ ውጪውን እንዲያዩ በማድረግ ግፍ ተፈፅሞባቸዋል። ይህ ክፍል 0.2 ሜትር ካሬ ያልበለጠ የአየር ማስገቢያ ብቻ የነበረው ነው።

- የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች ቀይ መስቀልን የመሳሰሉ ተቋማት እንዲጎበኙ ያቀረቡትን ጥያቄ ስላቅ በተሞላበት ሁኔታ ጨለማና ቀዝቃዛ ቤት በሚባል ቦታ ታስረው ብርሃን የማየትና ለመሳሰሉት የጤንነት ችግሮች ተጋልጠዋል።

- በምርመራም ወቅት ያልሰሩትን ወንጀል ፈፅሞ ያልሰሩትን ነገር በድብደባ በማስፈራራት፣ በማባባል ከላይ የተጠቀሱትን ተፅዕኖ ተፈፅሞባቸዋል።

- ለአለፉት 4 ሳምንታት ትኋን ቅማል ቁንጫ በሞላባቸው ክፍሎች ከአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞችና የእጅ አመለኞች ጋር (በጠቅላላ 150 በላይ) በመሆን የታጎሩ ሲሆን ገላ ለመታጠብ ለአንድ ሻወር በመሰለፍ ሥቃይ በማየት ላይ ይገኛሉ።

- እነዚህ የህሊና እስረኞች ቤተሰብና ዘመድ በአግባቡና በበቂ ደረጃ ሊጠይቃቸው አይችልም። የአብዛኞቹ ቤተሰብ የሚያስተዳድሯቸው ድርጅቶች በከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን ሁሉ በቁጭት ሲናገሩ ማጥመድ የተለመደ ነው።

- በብርበራው ወቅት በርካታ የቢሮ መገልገያዎች (ኮምፒተሮች፣ የፋክስ ማሽንና እስካነር) እንዲሁም የሥራ ሰነዶች ካላንዳች ጥንቃቄ ተሰብስበው በመወሰዳቸውና እስከዛሬም ባለመመለሳቸው በድርጅቶቻቸው ላይ ከፍተኛ ውድመት እየደረሰ መሆኑን ለአስተዳደር በየጊዜው ከሚያቀርቡት የአቤቱታ ማመልከቻ መረዳት ችዬአለሁ።

- እስካሁን ድረስ አራት ጊዜ የአስራ አራት ቀን ቀጠሮ በፍ/ቤት ህግ ከሚፈቅደው ውጪ ለፖሊሶች ተፈቅዶ ፖሊስ በአገኘው አጋጣሚ ፍ/ቤቱም የዋስ መብት በመከልከል እነዚህን አዛውንቶችንና ወጣቶችን በማጉላላት ላይ ይገኛሉ። በዚህም ምክንያት እስረኞቹ በፍ/ቤቱ ላይ የአላቸው ተስፋ ተሟጧል፤ በዚህ ስቃይ ውስጥ የሚገኙ በርካታ እስረኞች መኖራቸው የታወቀ ነው።

- ከነዚህ አዛውንቶችና ወጣቶች ውስጥ አንድም ቀን ወታደሮች ሆነው የማያውቁትን በወታደርነትና መኮንንነት ሲጠረጠሩ ሲቪል መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ እንኳን ፖሊስ በፈጠራ ወንጀል መቀጣቱ በጣም የሚያሳዝን እውነታ ነው።

- የእነዚህም እስረኞች ህይወት ቤተሰብ አቋቁመው የሚመሯቸው ድርጅቶች ከፍተኛ አደጋ ላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የአለም ህብረተሰብ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ለነፃነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ። በአሁኑ ወቅት እየደረሰ ስላለው ችግርና አደጋ የነዚህ ሰለባዎች ቤተሰቦች እውነተኛ ምስክርነት የሚሰጡ ስለሆነ እነሱን ማነጋገር ይቻላል።

በአሁኑ ወቅት በዋስ ተፈትቼ እቤቴ ተደብቄ እገኛለሁ። በዚህ እስር ሰቆቃ ከሚገኙ እስረኞች የሚከተሉትን አስታውሳለሁ፤

1. አቶ ብርሃኑ ሞገስ
2. አቶ አማረ ለማ
3. ሻለቃ አርጋው ካብታሙ
4. አቶ ተስፋዬ ደርቤ
5. አቶ ማህትመ በኩረ
6. አቶ መላኩ ተፈራ
7. አቶ ያሬድ ግርማ
8. ጋዜጠኛ ታድዮስ ታንቱ
9. ጋዜጠኛ ጎሹ ሞገስ
10. አቶ ለገሰ ኃ/ሚካኤል
11. አቶ ጉልማ ዳባ
12. አቶ ዮሐንስ ጌታሁን
13. አቶ ሽዋጉልት ይመኑ
14. አቶ ሽዋረጋ አሰግደው
15. አቶ ዳዊት አስግደው
16. ፎቶግራፈር ደረጀ እርገጤ

- በግድና በኃይል የኢንተርኔት፣ የኮምፒውተር፣ የሞባይል ፓስወርድ አስገድዶ በመውሰድ የግልና የድርጅትን ሚስጥርን ከማየት በተጨማሪ ለመወንጀያ የሚሆኑ ፅሁፎችን አስገብተው ለመወንጀል ጥረት ተደርጓል።
- ለፈጠራ ክሳቸው ውንጀላ ሲያጡ አስሮ ማስረጃ መፈለግና ከክፍል ክፍል ሲቀያይሩን በልዩ ልዩ መደለያ የማናቃቸውን እስረኞች በቅድሚያ በክፍል ውስጥ በማስቀመጥ መረጃ ከታሳሪዎች እንዲያገኙና የኃሰት ምስክርና መረጃ እንዲሰጡ ተደርገዋል።
- ሌላው ይህ ኦፕሬሽን በአብዛኛው ከሰሜን ሸዋ ተወላጆች ላይ ያተኮረ ሲሆን እንዲሁም ከአንድ ቤተሰብ እስከ 6 የሚደርሱ አዛውንቶች አስረው በማሰቃየት ላይ ይገኛሉ።

---

ከኢትዮሚድያ ዝግጅት - በእጅ ተፅፎ የደረሰንን ሪፖርት ታይፕ ስናደርግ ጥቂት ሊነበቡ ያልቻሉ ቃላቶችን ትተናቸዋል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የመለስ ዜናዊ ስርአት በወገን ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ እንደፀሃፊው ምኞት በጥራት ለኢትዮጵያዊ ወገናችን ለማድረስ ማክረናል። በዚሁ አጋጣሚ ይህ መልእክት በእንግሊዝኛና በሌሎች ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እንዲደርስ ችሎታው ያላችሁ ወገኖች ሃላፊነቱን እንድትወሰዱ ኢትዮሚድያ ከወዲሁ ጥሪውን ያቀርባል።

April 20, 2006
www.ethiomedia.com